**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ**

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# *CENTRAL STATISTICAL AGENCY*


## *የአገር አቀፍና የክልሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች*

***የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም.***

*[ታህሳስ 2004= 100]*

*መረጃ ቁጥር 4*

***COUNTRY AND REGIONAL LEVEL CONSUMER PRICE INDICES***



***[December 2011 =100]***

***For the month of June 2013***

***Information No. 4***

***አዲስ አበባ***

***ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ.ም.***

***ADDIS ABABA***

***05 July 2013***


***Tel: 251-11-1 553011***

***Fax: 251-11-1550334.***

***Email: csa@ethionet.et***


RPiREP

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|


መግቢያ........................................................ 1
የወሩ ዋጋ ግሽበት ሁኔታ ........................................ 7

የዘንድሮውና የአምናው ተመሳሳይ ወሮች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሀዝ ንፅፅር በአገር አቀፍ ደረጃ ........................................ 10

የዘንድሮውና የአምናው ተመሳሳይ ወሮች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሀዝ ንፅፅር በአገር አቀፍና በክልሎች ደረጃ........................................ 11


## የሠንጠረዦች ዝርዝር


ሠንጠረዥ ሀ፡ በጥናቱ የተሸፈኑ ገበያዎችና በኢንዴክስ ማዕቀፍ የተካተቱ ዕቃዎችና በዕቃዎች/አገልግሎቶች ብዛት በክልል........................................ 2

ሠንጠረዥ 1ሀ፡ ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች በአገር አቀፍ ደረጃ........................................ 13

ሠንጠረዥ 1ለ፡ ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስ በአገር አቀፍ ደረጃ........................................ 14

ሠንጠረዥ 1ሐ፡ አገር አቀፍ የቤት ኪራይ፣ የቤት መስሪያ ዕቃዎች፣ውሃና ኤነርጂ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛኤንዴክስ ........................................ 15

ሠንጠረዥ 2ሀ፡ ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስ በአገር አቀፍና በክልሎች ደረጃ ........................................ 16

ሠንጠረዥ 2ለ፡ የምግብ ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስ ማጠቃለያ በአገር አቀፍ እና በክልሎች ደረጃ ........................................ 18

ሠንጠረዥ 3ሀ፡ ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ........................................ 20

ሠንጠረዥ 3ለ፡ ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስ ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ........................................ 21

ሠንጠረዥ 4ሀ፡ ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለአፋር ክልላዊ መንግስት........................................ 22

ሠንጠረዥ 4ለ፡ ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስ ለአፋር ክልላዊ መንግስት........................................ 23

ሠንጠረዥ 5ሀ፡ ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለአማራ ክልላዊ መንግስት........................................ 24

ሠንጠረዥ 5ለ፡ ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስ ለአማራ ክልላዊ መንግስት........................................ 25

ሠንጠረዥ 6ሀ፡ ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኤንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት........................................ 26

ሠንጠረዥ 6ለ፡ ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ለቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት........................................ 27

ሠንጠረዥ 7ሀ: ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለድሬደዋ አስተዳደር ካውንስል ---------- 28

ሠንጠረዥ 7ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ለድሬደዋ አስተዳደር ካውንስል ---------- 29

ሠንጠረዥ 8ሀ: ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ---------- 30

ሠንጠረዥ 8ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የ ሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ለጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ---------- 31

ሠንጠረዥ 9ሀ: ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ---------- 32

ሠንጠረዥ 9ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ---------- 33

ሠንጠረዥ 10ሀ: ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ---------- 34

ሠንጠረዥ 10ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ---------- 35

ሠንጠረዥ 11ሀ: ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለደ.ኢ.ብ.ብ.ህ ክልላዊ መንግስት ---------- 36

ሠንጠረዥ 11ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለደ.ኢ.ብ.ብ.ህ ክልላዊ መንግስት ---------- 37

ሠንጠረዥ 12ሀ: ጠቅላላ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለሶማሌ ክልላዊ መንግስት ---------- 38

ሠንጠረዥ 12ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለሶማሌ ክልላዊ መንግስት ---------- 39

ሠንጠረዥ 13ሀ: ጠቅላላ የ ሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስና በስሩ የተካተቱ ክፍሎች ለትግራይ ክልላዊ መንግስት ---------- 38

ሠንጠረዥ 13ለ: ጠቅላላ ምግብና የምግብ ክፍሎች የ ሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ------41

# C O N T E N T S

**Page**

Introduction.......................................................................................................4

Inflation Rate…………………………………………………………………8

Comparison of CPI Movements, Current Vs Last Year's Similar Months, at country Level...............................................................................................10

Comparison of CPI Movements, Current Vs Last Year's Similar Months, at country and Regional Levels.........................................................................11

# List of Tables

Table a: Number of Markets Covered and Basket of Commodities by Region...........................................................................................................................2

Table 1a: General Consumer Price Index and Its Components at Country Level.........................................................................13

Table 1b: Consumer Price Index of Total Food and Its Components at Country Level.........................................................................14

Table 1c: Consumer Price Index of House Rent, Construction Materials, Water, Fuel and Power and Its Components at Country Level........................................................................15

Table 2a: Summary of General Consumer Price Indices at Country and Regional Levels..........................................................................16

Table 2b: Summary of Consumer Price Indices of Food at Country and Regional Levels..........................................................................18

Table 3a: General Consumer Price Index and Its Components for the City of Addis Ababa Administration...........................................20

Table 3b: Consumer Price Index of Total Food and Its Components for the City of Addis Ababa Administration...........................................21

Table 4a: General Consumer Price Index and Its Components for the Afar Regional State....................................................................22

Table 4b: Consumer Price Index of Total Food and Its Components for the Afar Regional State....................................................................23

Table 5a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Amhara Regional State.................................................................24
Table 5b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Amhara Regional State.................................................................25
Table 6a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Benishangul-Gumuz Regional State............................................26
Table 6b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Benishangul-Gumuz Regional State............................................27
Table 7a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Dire Dawa Administrative Council..............................................28
Table 7b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Dire Dawa Administrative Council..............................................29
Table 8a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Gambela Peoples Regional State..................................................30
Table 8b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Gambela Peoples Regional State..................................................31
Table 9a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Harari Peoples Regional State......................................................32
Table 9b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Harari Peoples Regional State......................................................33
Table 10a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Oromia Regional State..................................................................34
Table 10b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Oromia Regional State..................................................................35
Table 11a: General Consumer Price Index and Its
Components for the SNNP Regional State....................................................................36
Table 11b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the SNNP Regional State....................................................................37
Table 12a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Somali Regional State...................................................................38
Table 12b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Somali Regional State...................................................................39
Table 13a: General Consumer Price Index and Its
Components for the Tigray Regional State...................................................................40
Table 13b: Consumer Price Index of Total Food and Its
Components for the Tigray Regional State...................................................................41

## መግቢያ

የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ማለት ሸማቾች ለተወሰኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የከፈሉትን አማካይ የዋጋ ለዉጥ ለመለካት የሚያገለግል ጠቋሚ አሀዝ ነዉ። የዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ አብዛኛዉን ጊዜ መሠረት የሚያደርገዉ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ዉጤት በሆነዉ ቤተሰቦች በዕቃዎችና ግልጋሎቶች ለይ ባወጡት የመቶኛ ድርሻ መጠንና የወቅቱ የገበያ ዋጋ ላይ ነዉ። በዚህ ሪፖርት ዉስጥ የተካተቱት 12 ኢንዴክሶች (የ11 ክልሎችና የአገር አቀፍ) መሠረት ያደረጉት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በ2003 በጀት ዓመት በመላ አገሪቱ በናሙና በተመረጡ ቦታዎች ያካሔደዉን የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ዉጤት ነዉ።

ይህ ታህሳስ ወር 2004 ዓ.ምን መሠረት ያደረገው (ታህሳስ 2004=100) የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ በክልል ደረጃ ሲዘጋጅ በዓይነቱ ለሦስተኛ ጊዜ የተዘጋጀ ሲሆን በታህሣሥ 1999 ዓ.ም. መሠረት ያደረገውን የሸማቾች መመዘኛ ኢንዴክስ የሚተካ ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ ከ1988 ጀምሮና በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ደግሞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ተመሳሳይ ኢንዴክሶች እየተዘጋጁ ለተጠቃሚዎች ሲሰራጩ መቆየታቸዉ ይታወቃል። እነዚህ 12 የዋጋ መመዘኛ እንዴክሶች በአገሪቱ የሚገኙ 11 ክልሎችና የአገር አቀፉን ሪፖርት ጨምሮ የሚሸፍነዉ የዕቃዎችና የአገልግሎቶችን ክምችት በያዙ ሁለት ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው። እነሱም፡- የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ መመዘኛ ኢንዴክሶች ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ መመዘኛ ኢንዴክስ እንደገና በ11 ንዑስ ክፍሎች ይከፈላል። እነዚህም መጠጥ፣ሲጃራና ትምባሆ፣ ልብስና መጫሚያ፣ የቤት ኪራይ፣ የቤት መሥሪያ ዕቃዎች፣ ዉሃና ኢነርጂ፣ የቤት ዕቃዎች፣ የቤት ማስገጫዎች፣ የቤት ቁሳቁስና የቤት ሠራተኛ ደመወዝ፣ ሕክምና፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛ፣ መዝናኛና ባህል፣ ትምህርት፣ሬስቶራንትና ሆተሎችእንዲሁም ሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሲሆኑ የሁሉም ክፍሎች አጠቃላይ ውጤት የሚሆነዉ ደግሞ የጠቅላላ ዋጋዎች መመዘኛ እንዴክስ ነዉ።

በሁሉም ክልሎች የጠቅላላ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ስሌት አብዛኛዉን የመቶኛ ወጪ ድርሻ የሚይዘው የምግብና አልኮል ያልሆኑ መጠጦች መመዘኛ ኢንዴክስ ሲሆን በሁሉም የምግብ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዋና ዋና ክፍሎች ዳቦና እህል፣ ሥጋ፣ ወተት፣ አይብና ዕንቁላል፣ ዘይትና ቅባቶች፣ ፍራፍሬ፣ አትክልትና ጥራጥሬ፣ ስኳር ማርና ቸኮሌት፣ ሌሎች ምግቦችና አልኮል ያልሆኑ መጠጦች ናቸው።

ለዋጋ ኢንዴክሶቹ የተመረጡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የዋጋ መረጃ የሚሰበሰበው በየዞኑ/ በየልዩ ወረዳ በናሙና በተመረጡ ወካይ ከተሞች ዉስጥ ባሉ የገበያ ቦታዎች ነዉ። በመሆኑም ከእያንዳንዱ ዞን ሁለት ከተሞች (የገበያ ቦታዎች) የተመረጡ ሲሆን እንደዚሁም በእያንዳንዱ ልዩ ወረዳ አንድ ከተማ (የገበያ ቦታ) በጥናቱ እንዲካተት ተደርጓል።

በእነዚህ ከተሞች ዉስጥ ተመድበው ለሚሰሩ መረጃ ሰብሳቢዎች በየበጀት ዓመቱ

መጨረሻ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ላይ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ለአሰባሰቡ የሚረዱ የመስክ መገልገያ መሣሪያዎች (ሚዛን፣ ሜተር ... ወዘተ) ይሰጣቸዋል:: እነዚህ መሣሪያዎችን በመጠቀም በየወሩ የዋጋ መረጃዎችን ከነጋዴዎች ይሰበስባሉ:: አንዳንድ ጊዜም አንድ በላተኛ ወይም ገዢ ከነጋዴ ሲገዛ ቢገኝና ለሥራው ተባባሪነቱን ካሳየ መረጃው ከርሱም ይሰበሰባል:: የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰበዉ እንደ አዉሮፓዉያን ዘመን አቆጣጠር ወሩ በገባ ከ1ኛዉ ቀን አንስቶ አስከ 15ኛዉ ቀን  ነዉ:: የክልል ኢንዴክስን ለማስላት ለኢንዴክስ ለተመረጡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች አማካይ የችርቻሮ ዋጋቸውን የጂኦሜትሪክ ሚን ዘዴ ጥቅም ላይ ውሎአል:: የኢንዴክስ ሪፖርቱም በየወሩ ለተጠቃሚዎች በዚህ መልክ ይቀርባል::

የአገር አቀፍ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ የሚሰላው እያንዳንዱ ክልል ለአገር አቀፉ የቤተሰብ ወጪ ያለዉን የመቶኛ ድርሻ መሠረት በማድረግ ነዉ:: በመሆኑም ለአገር አቀፉ ኢንዴክስ ሰሌት ከ94 በመቶ በላይ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ክልሎች በቅደም ተከተል ኦሮሚያ፣ አማራ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ አዲስ አባባና ትግራይ ሲሆኑ የተቀሩት ክልሎች በየወሩ ለሚታየዉ አገር አቀፍ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ስሌት የሚኖራቸዉ አስተዋጽኦ ከስድስት በመቶ የማይበልጥ ነው::

ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት በአጠቃላይ 119 የገበያ ቦታዎች የተመረጡ ሲሆን በእያንዳንዱ ክልል የተመረጡ የናሙና ገበያዎች ብዛትና በየኢንደክሶቻቸዉ ማዕቀፍ የተካተቱ ዕቃዎች/አገልግሎቶች ብዛት ከዚህ በታች ቀርቦአል::

ሠንጠረዥ ሀ: በጥናቱ የተሸፈኑ ገበያዎችና በኢንዴክስ ማዕቀፍ የተካተቱ ዕቃዎች/ አገልግሎቶች ብዛት በክልል

**Table A: Number of Markets Covered and Basket of Commodities by Region**

| ተራ ቁጥር | ክልል | የገበያ ቦታዎች ብዛት | በኢንዴክስ የተካተቱ ዕቃዎች/ አገልግሎቶች ብዛት | | | Region |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ታህሳስ 1993=100 | ታህሳስ 1999=100 | ታህሳስ 2004=100 | |
| 1 | ትግራይ | 8 | 114 | 143 | 157 | Tigray |
| 2 | አፋር | 4 | 85 | 153 | 123 | Afar |
| 3 | አማራ | 20 | 118 | 144 | 160 | Amhara |
| 4 | ኦሮሚያ | 24 | 127 | 161 | 175 | Oromia |
| 5 | ሶማሌ | 6 | 85 | 122 | 120 | Somalie |
| 6 | ቤኒሻንጉል ጉምዝ | 6 | 111 | 142 | 164 | Benishangul-Gumuz |
| 7 | ደ.ብ.ብ.ህ | 31 | 130 | 152 | 168 | SNNP |
| 8 | ጋምቤላ | 3 | 105 | 103 | 131 | Gambela |
| 9 | ሐረሪ | 2 | 102 | 158 | 115 | Harari |
| 10 | አዲስ አበባ ከተማ | 12 | 175 | 193 | 165 | **Addis Ababa City** |
| 11 | ድሬዳዋ አስተዳደር | 3 | 121 | 150 | 139 | **Dire Dawa Administrative** |
| | **ድምር** | **119** | | | | **Total** |
| **Sr.No.** | | **Number of Markets** | **Basket of Commodities** | | | |

ለጠቋሚ አሀዙ ክንዋኔ ዋናዉ ነገር በጠቋሚ አሀዙ ማዕቀፍ ተካትተዉ በዋናነት የሚያገለግሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የመምረጥ ጉዳይ ነዉ፡፡ ጠቋሚ አሀዞች የሚመሠረቱት በአጠቃላይ በናሙና በሚመረጡ ዕቃዎች ላይ ሲሆን በጠቋሚ አሀዙ ማዕቀፍ ዉስጥ መካተት የሚገባዉ ዕቃ መወሰን ግን ሁሌም ቀላል የሚባል ተግባር አይደለም፡፡ የተለያየ የአመራረጥ ዘዴ መጠቀም ቢቻልም የሚመረጡት ዕቃዎች ለረጅም ጊዜ የሚኖራቸዉ ተፈላጊነት፤በአስተማማኝ ሁኔታ በገበያ ላይ የመገኘታቸዉ ጉዳይ፣ ሌሎችን ዕቃዎች የመወከል ብቃትና ከሌሎች ምርቶች ጋር ያላቸዉ ተወዳዳሪነት መሠረት ያደረገ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ በአጠቃላይ የተመረጡት ዕቃዎች በበቂ መጠን የመገኘታቸው ሁኔታ፣ በየወቅቱ ተወዳዳሪነታቸውና ዕቃዎችና አገልግሎቶች ምድቡን የመወከላቸው ብቃትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ታህሳስ 2004 ዓ.ም. መሠረት ያደረገው የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ አይነቶችና እያንዳንዱ ዋና ክፍል ያለው የወጪ ድርሻ በገፅ 6 ላይ ይታያል፡፡ ይህ ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው የምግብ የመቶኛ የወጪ ድርሻ ታህሳስ 1999 ዓ.ም. ከነበረው 57 በመቶ ወደ 53 በመቶ ቀንሷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ምግብ ነክ ያልሆነ መመዘኛ ኢንዴክስ ታህሳስ 1999 ዓ.ም. ከነበረው 43 በመቶ የወጪ ድርሻ ወደ 47 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ባጠቃላይ ሲታይ በሁሉም ክልሎች ኢንዴክስ ላይ የምግብ የወጪ ድርሻ የማይናቅ ቅናሽ ያሳየ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ የወጪ ድርሻ መጠነኛ እድገት አሳይታል፡፡

# Introduction

The Consumer Price Index (CPI) measures the average change in the price paid by consumers for a fixed market basket of goods and services. It is usually based on household expenditure weights of the goods and services in the basket and their current market prices. The twelve CPI's (i.e., the CPI's of the 11 Regions and the CPI at Country Level) presented in this report are based on the results of the Household Income, Consumption and Expenditure Survey (HICES) conducted by the Central Statistical Agency in 2010/2011 from which expenditure weights are derived for major household goods and services of that period and adjusted using the December 2011 retail prices of the goods and services as a base period.

The December 2011 based CPI updates the pervious CPI series (i.e. December 2006 based) and the newly selected baskets are more diversified and the weights are more accurate. It also showed various improvements and incorporates non-food index as an independent group. The new series is constructed for country as a whole and Regional States including Dire Dawa and the Addis Ababa City Administration. However, similar indices had been utilized at Addis Ababa Level since 1963 and at Country, Urban and Rural Levels since 1995/96 and in Country and Regional level since 2000.

All the twelve general indices are divided into two major groups that is food and non-food index. The non-food index has eleven major divisons each, namely: Alcoholic Beverages; Cigarettes and Tobacco; Clothing and Footwear; House Rent, Construction Materials, Water, and Fuel and Power; Furniture, Furnishing, Household Equipment and Operation; Health; Transport; Communication; Recreation, Culture; Education; Restaurants and Hotels; and Miscellaneous Goods and Services. On the other hand, the Food Index has 9 classes. These are: Bread and Cereals; Meat; Milk, Cheese and Eggs; Oil and Fats Spices; Fruits; Vegetables and Pulses, Sugar, Honey and Chocolate; Food Products n,e.c., and Non-alcoholic beverages.

Furthermore, the new CPI based on December 2011 also includes more detailed #Housing, Construction materials, Water and Fuel and Power; components.

For the construction of the current consumer price indices, up to date data on retail prices are collected in the purposely selected sample market places located in representative urban centers in each zone/special weredas of the country. Hence, a total of 119 market places were selected for the retail price survey. In each market place an enumerator is assigned to undertaking the data collection activities. The price data is collected from the 1st day though 15th days of European Calendar month under consideration. To calculate the monthly regional consumer price indices, geometric means of prices of the specific regions are used. The distribution of the market place of each region and items included in the basket of commodities are given on Table A on page 2.

An important factor in constructing a Consumer Price Index is to select the representative basket of goods and services. Including all consumption items into the market basket of goods and services is both cumbersome and unnecessarily costly in term of data collection and processing. Furthermore, it doesn't make sense to include an insignificant weight into an index basket which could not move the price relative up or downwards compared to the general market trend. As a result, basket of goods and services included in the regional baskets are determined by expenditure cut-off point. The total numbers of items included in the regional basket in the December 2011 based indices are given in Table A on page 2.

Country level CPI aggregates the regional group indices and the contributions of the five relatively big regions in terms of the magnitude of the expenditure account for more than 94 percent. These regions are Oromiya, Amhara, SNNP, Addis Ababa and Tigray. On the other hand, the contributions of the remaining regions to the Country Level Consumer Price Index is about six percent.

According to the weights for food and non-food groups in Table B below, the December 2011 based CPI is about 53 percent of household expenditure spent on the food component, which declined by 4 percentage points as compared to the December 2006 based CPI. On the other hand, the expenditure on non-food components increased from 43 percent to 47 percent.

The 2011 CPI adapted the full version of the latest Classification of Individual Consumption by Purpose (COICOP) while the 2006 based CPI was an earlier version of COICOP. The following table shows the different CIOICOP versions by Comparison. In the 2006 based CPI Recreation, Entertainment and Education; and Transport and Communication were put in the same divisions while the 2011 based CPI separated them as standalone divisions. A new division called Restaurants and Hotels was introduced in the 2011 based CPI by moving the food taken away from home previously categorized with Food to this new division. Non-Alcoholic beverages were taken out of the Non-Food division and moved to the Food division.

**Table B: Major groups in the 2006 and 2011 based CPI and their weights at Country Level**

| Comparison of COICOP Divisions(2006 Vs 2011) | December 2006=100 | December 2011=100 |
|---|---|---|
| 1. FOOD AND NON-ALCOHOLIC BEVERAGES | 57% | 53% |
| **Non - FOOD** | 43% | 47% |
| **2. ALCOHOLIC BEVERAGES AND TOBACCO, NARCOTICS** | 2.5 | 4.85 |
| **3. CLOTHING AND FOOTWEAR** | 8.32 | 6.62 |
| **4. HOUSING, WATER, ELECTRICITY, GAS AND OTHER FUELS** | 20.56 | 16.34 |
| **5.FURNISHINGS, HOUSEHOLD EQUIPMENT AND ROUTINE MAINTENANCE OF THE HOUSE** | 3.75 | 5.41 |
| **6. HEALTH** | 1.11 | 1.08 |
| **7. TRANSPORT** | 2.5 | 2.80 |
| **8. COMMUNICATION** | - | 1.08 |
| **9. RECREATION AND CULTURE** | 1.1 | 0.60 |
| **10. EDUCATION** | - | 0.45 |
| **11. RESTAURANTS AND HOTELS** | - | 5.46 |
| **12. MISCELLANEOUS GOODS AND SERVICES** | 3.2 | 2.56 |
| **Total** | 100 | 100 |

# *የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም. የዋጋ ግሽበት ሁኔታታ*

## *ሀ) <u>የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ አገራዊ የዋጋ ግሽበት</u>*

ከሠንጠረዥ #ሐ; መረዳት እንደሚቻለው በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም. የተመዘገበው የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ13.5 በመቶ ጭማሪ አሳይቶአል:: በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም. አገራዊ የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ የምግብ የዋጋ ግሽበት በ12.6 ከመቶ ዕድገት አሳይቶአል:: የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ አገራዊ ምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበትም በ14.8 ከመቶ ጭማሪ አሳይቶአል:: *የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ የዋጋ ግሽበት ረዘም ያለ ጊዜ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ የሚያሳይ ነው::*

## *ለ) <u>የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር በማነፃፀር</u>*

*የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር* በማነፃፀር የሚገኘው ውጤት ወቅታዊ የዋጋ ግሽበት ሁኔታን ይገልጻል:: ሠንጠረዥ (መ) የሚያሳየው የዋጋ ግሽበት ሁኔታ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር በማነፃፀር ነው:: ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ካለፈው ዓመት ሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር በ7.4 ከመቶ ከፍ ብሎአል:: ለዚህ ጭማሪ ምክንያቱ በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም የተመዘገበው አጠቃላይ የዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ 119.6 ከመቶ በሰኔ ወር 2004 ከተመዘገበው 111.4 ከመቶ አጠቃላይ የዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ በልጦ በመገኘቱ ነው:: የምግብ ዋጋ ግሽበት የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም ካለፈው ዓመት የሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር በ3.7 ከመቶ ጭማሪ አሳይቶአል:: ለዚህ ጭማሪ ምክንያቱ በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም የተመዘገበው የምግብ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ 120.1 ከመቶ በሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ከተመዘገበው 115.9 ከመቶ የምግብ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ በልጦ በመገኘቱ ነው:: ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻፀር የዳቦና እህል ዋጋ ግሽበት በ8.0 ከመቶ ጭማሪ በማሳየቱ ለምግብና ለአጠቃላይ ዋጋ ግሽበት መጨመር ዋነኛው ምክንያት ሆኖአል:: በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም ከምግብ ክፍሎች ዘይትና ቅባቶች፤ ሌሎች ምግቦች እና አልኮል ያልሆኑ መጠጦችና ቡና መጠነኛ ቅናሽ አሳይተዋል:: ምግብ ነክ ያልሆኑ የኢንዴክሱ ክፍሎች የዋጋ ግሽበት የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም ካለፈው ዓመት ሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸርም የ11.9 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል:: ምግብ ነክ ያልሆኑ የኢንዴክሱ ክፍሎች የዋጋ ግሽበት ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻፀር ከፍ እንዲል ካደረጉት ዋና ምክንያቶች ውስጥ በልብስና መጫሚያ፣ የማገዶ እንጨት፣ የቤት ዕቃዎችና የቤት ማሰገጫዎች ላይ የታየው የዋጋ ጭማሪ ነው:: ትራንስፖርት የቀነሰ ሲሆን ኮሙኒኬሽን ኢንዴክስ ላይ ምንም ለውጥ አልታየም::

## *ሐ) <u>የዋጋ ግሽበት ሁኔታ የአሁኑን ወር ካለፈው ወር ጋር በማነፃፀር</u>*

የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት ካለፈው ግንቦት ወር 2005 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር በ0.7 ከመቶ ጭማሪ አሳይቶአል:: ወርሃዊ የዋጋ ግሽበት ምጣኔው በመጨረሻዎቹ ሁለት ተከታታይ ወራት መካከል ያለውን የዋጋ ለውጥ ለመለካት ያገለግላል:: ወርሃዊ የዋጋ ግሽበት ምጣኔው የወቅቱን ሁኔታ የሚሳይ በመሆኑ የአጭር ጊዜ ክስተቱን ብቻ ያመለክታል::

# ***June 2013** Country Level **Inflation Rate***

## *a) 12 months Moving Average Inflation at Country Level*

As it is indicated in Table 'C' below the country level overall inflation rate (annual change based on 12 months Moving Average) rose by 13.5 percent in June 2013 as compared to the one observed in a similar period a year ago. The country level food inflation increased by 12.6 percent as compared to the one observed a year ago. The country level Non-food inflation rate increased by 14.8 percent in June 2013 as compared to the one observed in June 2012. The 12 months moving average inflation rate shows the longer term inflationary situation.

## *b) Inflation based on comparison of Current vs. Last year's similar month at Country Level*

Inflation based on comparison of Current vs. Last year's similar month shows the current inflation situation. Table (D) shows Inflation rate based on last year's similar month comparison. As can be seen from the table the June 2013 General year-on-year inflation has increased by 7.4 percent as compared to the one observed in June 2012. The 7.4 percent rise in General inflation rate is due to the fact that the General Consumer Price Index (CPI) of 119.6 percent observed in June 2013 was higher than the corresponding 111.4 percent General Consumer Price Index (CPI) observed in June 2012. The year-on-year Food inflation has increased by 3.7 percent in June 2013 as compared to the one observed in June 2012. The reason for the increase in the food Inflation rate was that the 120.1 percent Food Consumer Price Index (CPI) observed in June 2013 was greater than the corresponding 115.9 percent Food Consumer Price Index (CPI) observed in June 2012. The total price index of Bread and Cereals in June 2013 has increased by 8.0 percent as compared to similar month last year which significantly contributed to the rise in the indices of Food and the General Consumer Price Index. Oils and fats and Non-alcoholic Beverages and Coffee have declined by 2.4 percent, Food products n.e.c; by 0.9 percent and 11.3 percent, respectively. Moreover, the Non-Food inflation also increased i.e by 11.9 percent in June 2012 as compared to the one observed in June 2012. Rise in Inflation in the Non-food component is mainly due to rise in the prices of Clothing and Footwear, Firewood and Household goods and furnishings. However, Transport has slightly declined by 2.9 percent in June 2013 as compared to June 2012. There was no change in the Index of communication as compared to similar month last year.

## *c) Inflation based on comparison of Current vs. Last month at Country Level*

*The General CPI for June 2013 has showed an increase of 0.7 percent as compared to the preceding month of May 2013. The monthly inflation rate measures the price change between the two latest months. Although up to date, it can be affected by seasonal and other short term effects.*

ሠንጠረዥ ሐ: <u>በአገር አቀፍ ደረጃ *የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ*</u>

**Table C: <u>The Country Level 12 months Moving Average Inflation Rate</u>**

| በጀት ዓመት (ወር) | የዋጋ ግሽበት ሁኔታ | | | **Budget Year and months** |
|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት | የምግብ የዋጋ ግሽበት | የምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበት | |
| <u>በጀት ዓመት በወራት</u> | | | | **Budget Year in Months** |
| ዓመታዊ አማካይ<br>ሐምሌ 2004 - ሰኔ 2005 | | | | Annual Average<br>July 2012 – June 2013 |
| | | | | |
| ***ሰኔ 2004*** | 34.1 | **42.9** | **22.4** | June 2012 |
| ***ሐምሌ 2004*** | 32.5 | **40.7** | **21.6** | July 2012 |
| ***ነሐሴ 2004*** | 30.9 | **38.5** | **20.8** | August 2012 |
| ***መስከረም 2005*** | 29.3 | **36.1** | **20.5** | September 2012 |
| ***ጥቅምት 2005*** | 27.5 | **33.2** | **20.3** | October 2012 |
| ***ኅዳር 2005*** | 25.8 | **30.5** | **19.9** | November 2012 |
| ***ታህሳስ 2005*** | 24.1 | **28.1** | **19.3** | December 2012 |
| ***ጥር 2005*** | 22.3 | **25.6** | **18.5** | January 2013 |
| ***የካቲት 2005*** | 20.3 | **22.6** | **17.7** | February 2013 |
| ***መጋቢት 2005*** | 18.2 | **19.7** | **16.7** | March 2013 |
| ***ሚያዝያ 2005*** | 16.2 | **16.7** | **16.0** | April 2013 |
| ***ግንቦት 2005*** | 14.6 | **14.4** | **15.1** | May 2013 |
| ***ሰኔ 2005*** | 13.5 | **12.6** | **14.8** | June 2013 |
| *Budget Year* | *Inflation Rate* | | | |
| | **Overall Inflation Rate** | **Food Inflation Rate** | **Non-food Inflation Rate** | |

**ሠንጠረዥ መ፡ የዘንድሮውና የአምናው ተመሳሳይ ወሮች የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለውጥ ንፅፅር በአገር አቀፍ ደረጃ ማጠቃለያ**

**Table D: Summary of *Comparison of CPI Movements, Current vs. Last year's Similar Months at Country Level***

| በጀት ዓመት (ወር) | የዋጋ ግሽበት ሁኔታ | | | Budget Year and months |
|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት | የምግብ የዋጋ ግሽበት | የምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበት | |
| <u>በጀት ዓመት በወራት</u> | | | | **Budget Year in Months** |
| ዓመታዊ አማካይ<br>ሐምሌ 2004 - ሰኔ 2005 | | | | Annual Average<br>July 2012 – June 2013 |
| | | | | |
| ሰኔ 2004 | 20.8 | **25.4** | **15.8** | June 2012 |
| ሐምሌ 2004 | 21.5 | **24.9** | **17.7** | July 2012 |
| ነሐሴ 2004 | 21.6 | **25.2** | **18.2** | August 2012 |
| መስከረም 2005 | 21.3 | **22.9** | **20.5** | September 2012 |
| ጥቅምት 2005 | 17.9 | **17.4** | **20.0** | October 2012 |
| ኅዳር 2005 | 17.9 | **17.1** | **19.5** | November 2012 |
| ታህሳስ 2005 | 14.9 | **15.2** | **14.5** | December 2012 |
| ጥር 2005 | 12.7 | **12.7** | **12.6** | January 2013 |
| የካቲት 2005 | 10.9 | **9.3** | **12.7** | February 2013 |
| መጋቢት 2005 | 7.6 | **5.2** | **10.5** | March 2013 |
| ሚያዝያ 2005 | 6.1 | **1.6** | **11.5** | April 2013 |
| ግንቦት 2005 | 6.3 | **3.4** | **9.8** | May 2013 |
| ሰኔ 2005 | 7.4 | **3.7** | **11.9** | June 2013 |
| *Budget Year* | *Inflation Rate* | | | |
| | **Overall Inflation Rate** | **Food Inflation Rate** | **Non-food Inflation Rate** | |

**ሠንጠረዥ ሠ: የአሁኑናና ያለፈው ወር የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለውጥ ንፅፅር በአገር አቀፍ ደረጃ ማጠቃለያ**

**Table E: Summary of *Comparison of CPI Movements, Current vs. Last month at Country Level***

| በጀት ዓመት (ወር) | የዋጋ ግሽበት ሁኔታ | | | Budget Year and months |
|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት | የምግብ የዋጋ ግሽበት | የምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበት | |
| በጀት ዓመት በወራት | | | | **Budget Year in Months** |
| ዓመታዊ አማካይ ሐምሌ 2004 - ሰኔ 2005 | | | | Annual Average July 2012 – June 2013 |
| | | | | |
| ሰኔ 2004 | -0.3 | **0.0** | **-0.7** | June 2012 |
| ሐምሌ 2004 | 1.1 | **0.1** | **2.2** | July 2012 |
| ነሐሴ 2004 | 1.8 | **2.8** | **0.7** | August 2012 |
| መስከረም 2005 | 2.3 | **1.6** | **3.2** | September 2012 |
| ጥቅምት 2005 | -0.9 | **-2.3** | **0.8** | October 2012 |
| ኅዳር 2005 | -0.3 | **-1.3** | **0.8** | November 2012 |
| ታህሳስ 2005 | -0.8 | **-1.4** | **-0.2** | December 2012 |
| ጥር 2005 | 0.3 | **0.5** | **0.1** | January 2013 |
| የካቲት 2005 | 0.6 | **-0.3** | **1.5** | February 2013 |
| መጋቢት 2005 | 0.6 | **1.0** | **0.1** | March 2013 |
| ሚያዝያ 2005 | 0.7 | **-0.3** | **1.7** | April 2013 |
| ግንቦት 2005 | 1.0 | **2.9** | **-1.0** | May 2013 |
| ሰኔ 2005 | 0.7 | **0.3** | **1.2** | June 2013 |
| *Budget Year* | *Inflation Rate* | | | |
| | **Overall Inflation Rate** | **Food Inflation Rate** | **Non-food Inflation Rate** | |

## *የዘንድሮውና የአምናው ተመሳሳይ ወሮች የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሀዝ ንፅፅር በአገር አቀፍ ደረጃ*

## *Comparison of CPI Movements, Current vs Last year's Similar Months at Country Level*

*ከሠንጠርዥ 1(ሀ) መረዳት እንደሚቻለው የሰኔ ወር 2005 ዓ.ም የአገር አቀፍ ጠቅላላ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ ከሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ጠቅላላ ኢንዴክስ ጋር ሲነፃፀር በ7.4 ከመቶ ጭማሪ አሳይቶአል:: ለዚህ ጭማሪ ምክንያት የሆኑት ምግብና አልኮል ያልሆኑ መጠጦች 3.7 ከመቶ፣ መጠጥ፣ ሲጃራና ትምባሆ በ12.2 ከመቶ፣ ልብስና መጫሚያ በ10.1 ከመቶ፣ የቤት ኪራይ፣ የቤት መሥሪያ ዕቃዎች፣ ዉሃና ኢነርጂ በ14.2 ከመቶ፣ የቤት ዕቃዎች፣ ቤት ማስገጫዎች፣ የቤት ቁሳቁስና የቤት ሠራተኛ ደመወዝ በ12.9 ከመቶ፣ ህክምና 26.4 ከመቶ፣ መዝናኛና ባህል በ5.3 ከመቶ፣ ትምህርት በ1.0 ከመቶ፣ ሬስቶራንትና ሆተሎች በ15.2 እና ሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች 9.4 ከመቶ በየኢንዴክሶቻቸው ላይ ጭማሪ በማሳየታቸው ነው:: በሌላ በኩል ትራንስፖርት በ2.9 ከመቶ ቅናሽ አሳይቶአል:: መገናኛ ምንም ለውጥ አላሳየም::*

*The June 2013 Country Level Consumer Price Index has increased by 7.4 percent as compared to June 2012 (Table 1(a)). This increase in the General Consumer Price Index is attributed to the rise observed in the indices of Food and Non-alcoholic beverages 3.7 percent, Alcoholic Beverages and Tobacco 12.2 percent, Clothing and Footwear by 10.1 percent, House Rent, Construction Materials, Water and Fuel and Power by 14.2 percent, Furniture, Furnishings, Household Equipment and Operation by 12.9 percent, Health by 26.4 percent, Recreation and Culture 5.3 percent, Education by 1.0 percent, Restaurant and Hotels 15.2 percent and Miscellaneous Goods by 9.4 percent . On the other hand, Transport has declined by 2.9 percent. No change was observed in the index of Communication.*

*ሠንጠረዥ 1(ለ) እንደሚያሳየው ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ጋር ሲነፃር አብዛኞዎቹ የምግብ ክፍሎች ጭማሪ አሳይተዋል:: በተለይም ዳቦና እህል በ8.0 ከመቶ፣ ሥጋ በ12.8 ከመቶ፣ ወተት፣ አይብና ዕንቁላል በ8.5 ከመቶ፣ ፍራፍሬ በ12.4 ከመቶ፣አትክልት፣ ጥራጥሬ፣ ድንችና ሌሎች ስራ ስሮች በ1.1 ከመቶ እና ስኳር ማርና ቼኮሌት በ6.1 ከመቶ ዕድገት በየኢንዴክሶቻቸው ላይ አሳይተዋል:: በሌላ በኩል ዘይትና ቅባቶች በ2.4 ከመቶ፤ ሌሎች ምግቦች በ0.9 ከመቶ እና አልኮል ያልሆኑ መጠጦችና ቡና በ12.8 ከመቶ በኢንዴክሶቻቸው ላይ ቅናሽ አሳይተዋል::*

*Most of the components of Food index showed increase as compared to similar month last year (Table 1(b)). Specially, Bread and Cereals (8.0 percent), Meat (12.8 percent), Milk, Cheese and Eggs (8.5 percent), Fruits by (12.4 percent), Vegetables and Pulses, potatoes and Tubers by (1.1 percent) and Sugar, Jam, Honey, and Chocolate (6.1 percent). On the other hand, decline was observed in the indices of oils and Fats by (2.4 percent), and Food Products n.e.c (0.9 percent) and Non-Alcoholic beverages and Coffee by (12.8 percent).*